## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ *"የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የጉዳዮች አቀራረብና አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2012"* ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጉም

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) "ሕገ መንግስት" ማለት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት ማለት ነው፡፡

2) "አዋጅ" ማለት የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አዋጅ ቁጥር 798/2005 ማለት ነው፡፡

3) "ጉባኤ" ማለት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 82/1/ የተቋቋመው የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ነው፡፡

4) "ንኡስ አጣሪ ኮሚቴ" ማለት ከሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አባላት መካከል የሚመረጡ ከሶስት ያላነሰ አባላትን ያካተተ ኮሚቴ ነው፡፡

5) "ጽህፈት ቤት" ማለት በአዋጅ ቁጥር 798/2005 አንቀጽ 27/1/ መሰረት የተቋቋመው የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ጽ/ቤት ነው፡፡

6) "ፍርድ ቤት" ማለት የፌዴራል፣ የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር በማናቸውም ደረጃ ያለ ፍርድ ቤት ማለት ሲሆን ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ሲባል ሌሎች በሕግ የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸውን የፌደራል፣ የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር አካላትንም ያጠቃልላል፡፡

7) "የመንግስት አካል" ማለት የፌዴራል፣ የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር ሕግ አውጪ፣ ሕግ አስፈጻሚ እና ሕግ ተርጓሚ ነው፡፡

8) "ሕግ አስፈጻሚ" ማለት በሕገ መንግስቱ መሰረት ሕግ የማስፈጸም ስልጣን የተሰጣቸውን ማንቸውንም የመንግስት ተቋማት የሚያካትት ነው፡፡

9) "የሕገ መንግስት አቤቱታ" ማለት የአንድ የመንግስት አካል ወይም ባለስልጣን የመጨረሻ ውሳኔ በሕገ መንግስቱ የተረጋገጠን መብት ወይም ነጻነት ጥሷል በሚል ለጉባኤው የሚቀርብ አቤቱታ ነው፡፡

10)“የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ” ማለት በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 9 ከተመለከቱት የሕገ መንግስት ትርጉም ጉዳዮች ውጪ ባሉ በማናቸውም ሕገ መንግስታዊ ጉዳዮች ላይ የሚቀርብ የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ነው፡፡

11) “የመጨረሻ ውሳኔ” ማለት በየደረጃው ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ወይም ሌላ የመንግስት አካል ቀርቦ የተወሰነና ሂደቱን ያጠናቀቀ ማለት ነው፡፡

12) “ክልል“ ማለት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 47(1) መሰረት የተጠቀሱትን እና በሕገ መንግስቱ መሰረት የተቋቋሙትን ያጠቃልላል፡፡

13) “የከተማ አስተዳደር” ማለት የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደር ማለት ነው፡፡

14) “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

**3. የጾታ አገላለጽ**

ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ያካትታል፡፡

**4. የጉባኤው አርማና ማሕተም**

ጉባኤው በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት የተሰጡትን ተግባራትና ኃላፊነቶች የሚያንጸባርቁ አርማና ማህተም ይኖሩታል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የጉባኤው አወቃቀር

**5. የጉባኤው አወቃቀር**

ጉባኤው የሚከተለው መዋቅራዊ አደረጃጀት ይኖረዋል፡-

ሀ) ዋና ጉባኤ፣

ለ) ንኡስ አጣሪ ኮሚቴ፣ እና

ሐ) የጉባኤው ጽህፈት ቤት፡፡

**6. የንኡስ አጣሪ ኮሚቴ አሰያየም**

1) ጉባኤው ከሶስት ያላነሰ አባላት ያለው ንኡስ አጣሪ ኮሚቴ ይኖረዋል፡፡

2) የንኡስ አጣሪ ኮሚቴው አባላት በጉባኤው በምርጫ የሚሰየሙ ይሆናል፡፡ ጉባኤው ከንኡስ አጣሪ ኮሚቴው አባላት መካከል አንዱን በኮሚቴው ሰብሳቢነት ይሰይማል፡፡

3) የንኡስ አጣሪ ኮሚቴ ብዛትና የስራ ዘመን ጉባኤው ይወስናል፡፡

## ክፍል ሶስት

## የጉባኤው፣ የጉባኤው ሰብሳቢ፣ የንኡስ አጣሪ ኮሚቴና የጽ/ቤቱ ዝርዝር ተግባራት

ጉባኤው፣ የጉባኤው ሰብሳቢ፣ የንኡስ አጣሪ ኮሚቴውና ጽ/ቤቱ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስትና በአዋጅ ቁ. 798/2005 የተሰጣቸው ስልጣንና ተግባራት እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ክፍል የተዘረዘሩትን ተግባራት ያከናውናሉ፡፡

### 7. የጉባኤው ተግባራት

ጉባኤው የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡-

1) የንኡስ አጣሪ ኮሚቴ አባላትን በአዋጁ መሰረት ከአባላቱ መካከል መርጦ ይሰይማል፣ የተሰየሙት የንኡስ አጣሪ ኮሚቴው አባላት በተለያየ ምክንያት ሲጓደሉ ወይም ከኮሚቴው ስራ ሲነሱ እንዲተኩ ያደርጋል፣

2) በንኡስ አጣሪ ኮሚቴው ተለይተው የሚቀርቡለትን የተለያዩ ሪፖርቶችን፣ ውሳኔዎችንና የውሳኔ ኃሳቦችን ተገቢ ውይይት አድርጎ ያጸድቃል፣ እንደአስፈላጊነቱ ያሻሽላል፣ ተጨማሪ ጥናትና ማጣራት የሚፈልጉ ከሆነ የጥናትና የማጣራት ስራ እንዲደረግ ያዛል፣

3) አንድ የንኡስ አጣሪ ኮሚቴ አባል ከኮሚቴ አባልነት ለመነሳት አሳማኝ ምክንያት በማቅረብ ሲጠይቅ እና ጥያቄው በጉባኤው ተቀባይነት ሲያገኝ ወይም ጉባኤው በራሱ ተነሳሽነት የኮሚቴ አባሉ እንዲነሳ ሲወስን የአገልግሎት ዘመኑ ከማለቁ በፊት ሊያነሳው ይችላል፡፡

4) ለአንድ ለተወሰነ የማጣራት ተግባር ኃላፊነት የሚሰጠው ጊዜያዊ ኮሚቴ ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ያቋቁማል፡፡

### 8. የጉባኤው ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር

የጉባኤው ሰብሳቢ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) የጉባኤውን ስብሳባ አጀንዳዎች ያዘጋጃል ወይም ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ ያዛል፣ ይተገብራል፡፡

ለ) የጉባኤውን ስብሰባዎችና ውይይቶች በዚህ መመርያ መሰረት ይመራል፣ ይከታተላል፡፡

ሐ) የጉባኤውን እና የንኡስ አጣሪ ኮሚቴውን የስራ ሁኔታና አፈጻጸም እንዲሁም የስብሰባ አከባበር ስርዓት ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፡፡

መ) የጉባኤው አባላት፣ የጽ/ቤቱ ሃላፊዎችና ሰራተኞች የሚያደርጓቸውን ኦፊሴላዊ ጉዞዎች ያጸድቃል፡፡

ሠ) ጉባኤው የሚያስተላልፋቸው ውሳኔዎች እና ትእዛዞች መፈጸማቸውን ይከታተላል፡፡

ረ) ጉባኤው አስተዳደራዊ ኃላፊነቶቹን ለመወጣት እንደአስፈላጊነቱ የጉባኤውን አባላት እና የጽ/ቤቱን ሃላፊዎችና ሰራተኞች ያካተተ አስተዳደራዊ ኮሚቴዎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡ የየኮሚቴዎቹን ተግባርና ኃላፊነት እና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች ጉባኤው ኮሚቴዎቹን በሚያቋቁምበት ጊዜ አብሮ ሊወስን ይችላል፡፡

ሰ) የጉባኤውን፣ የንኡስ አጣሪ ኮሚቴን፣ የጽ/ቤቱን እና በጉባኤው የተቋቋሙ ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን ስራ በበላይነት ይከታተላል፣ ይመራል፡፡

## 9. የምክትል ሰብሳቢው ተግባር

1. የጉባኤው ሰብሳቢ በሌሉ ጊዜ የጉባኤውን ሰብሳቢ ስራ ተክቶ ይሰራል፡፡
2. በጉባኤው ሰብሳቢ ወይም በጉባኤው ተለይተው የተሰጡትን ዝርዝር ተግባራት ያከናውናል፡፡

## 10. የንኡስ አጣሪ ኮሚቴው ተግባራት

ንኡስ አጣሪ ኮሚቴው የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የሕገ መንግስት አቤቱታዎች ወይም ጥያቄዎች ላይ ቅድመ ማጣራት በማድረግ ጉዳዩ ሕገ መንግስታዊ ጉዳይ መሆኑንና አለመሆኑን ይለያል፡፡
2) የሕገ መንግስት ትርጉም የሚያስፈልጋቸውና የማያስፈልጋቸው ጉዳዮችን አጣርቶ ውሳኔ ወይም የውሳኔ ሀሳብ ለጉባኤ ያቀርባል፡፡

3) ለጉባኤው በሚቀርቡ ጉዳዮች ላይ ለውሳኔ የሚረዱ ጭብጦችን፣ አግባብነት ያላቸው ህጎችን፣ ውሳኔዎችንና አስፈላጊ ሲሆን አግባብነት ያላቸው ተሞክሮዎችን በሚያሳይ መልኩ ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡

4) አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ባለጉዳዮችን፣ አግባብነት አላቸው ብሎ የሚያምንባቸውን ተቋማት ወይም ባለሙያዎች አስቀርቦ ይሰማል፡፡

5) ጉዳዮችን ለማጣራት አስፈላጊ ነው ብሎ ያመነበትን ማንኛውም አይነት ማስረጃ አስቀርቦ ይመረምራል፡፡

6) በጽ/ቤቱ ተዘጋጅተው የሚቀርቡ ጥናቶችና የሙያ አስተያየቶች ላይ ውይይት ያደርጋል፣ ግብአት ይሰጣል፣ አስፈላጊ ሲሆንም ተጨማሪ ጥናት እንዲደረግ ሊያዝ ይችላል፡፡

7) ጉዳዮችን ከተመደቡለት የጽ/ቤቱ ጥናትና ምርምር ባለሙያዎች ጋር በመሆን ያጣራል፤ እንደአስፈላጊነቱም በአካል የመስክ ጉብኝት በማድረግ የማጣራት ስራውን ይከውናል፡፡

8) ጥናት እንዲደረግባቸው በንኡስ አጣሪ ኮሚቴው የተለዩ ጉዳዮች እንዲጠኑ ለጽ/ቤቱ አቅጣጫ ይሰጣል፣ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፡፡

**11.የንኡስ አጣሪ ኮሚቴ ሰብሳቢ ተግባርና ሃላፊነት**

1) የንኡስ አጣሪ ኮሚቴው ሰብሳቢ ከጽ/ቤቱ ጋር በመነጋገር የውይይት አጀንዳ ያዘጋጃል፣ እንደአስፈላጊነቱ ከስብሰባው በፊት ለአባላቱ እንዲሰራጭ ያደረጋል፣

2) የኮሚቴውን ስብሰባ ይመራል፣ በስብሰባው የተሰጡ የኮሚቴው ውሳኔዎችና ትእዛዞች መፈጸማቸውን ይከታተላል፡፡

3) ንኡስ አጣሪ ኮሚቴው ስራዎቹን በብቃት እንዲፈጽም የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

4) ሌሎች በጉባኤው የሚሰጡትን ስራዎች ያከናውናል፡፡

**12. የጽህፈት ቤቱ ተግባራት**

1) የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ወይም አቤቱታ ለማቅረብ የሚመጡ ባለጉዳዮችን ተቀብሎ ያስተናግዳል፤

2) በባለጉዳይ የቀረበው የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ወይም አቤቱታ ተሟልቶ መቅረቡን ያረጋግጣል፤ ተሟልቶ ሲቀርብ ፋይል ቁጥር በመስጠት መዝገብ ይከፍታል፡፡

3) ተሟልቶ ያልቀረበ ጥያቄ ወይም አቤቱታ ተሟልቶ እንዲቀርብ ለባለጉዳዩ ያሳውቃል፡፡

4) የጽ/ቤቱ የህግ ባለሞያዎችን በተመጣጣኝ ሁኔታ ለንኡስ አጣሪ ኮሚቴው ይመድባል፡፡

5) ከጉባኤው ሰብሳቢ በሚሰጠው የስራ ውክልና መሰረት የተከፈቱ መዝገቦችን ማጣራት እና ምርመራ እንዲደረግባቸው እንደአግባብነቱ ለጽ/ቤቱ የህግ ባለሙያዎች ወይም ለንኡስ አጣሪ ኮሚቴው ይደለድላል፡፡

6) ለጽ/ቤቱ የህግ ባለሙያዎች ወይም ንኡስ አጣሪ ኮሚቴው የተመሩ መዝገቦችን የውሳኔና የውሳኔ ሀሳብ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፡፡

7) ከባለጉዳይ የሚቀርቡ ወይም በጉባኤው እና በንኡስ አጣሪ ኮሚቴው እንዲቀርቡ የሚጠየቁ ተጨማሪ መረጃዎች እንዲሰበሰብ ያደርጋል፡፡

8) የጉባኤውን ውሳኔ፣ የውሳኔ ሃሳብ፣ ትዕዛዝ፣ ወይም ሌሎች አቅጣጫዎች ለሚመለከታቸው አካላት ያደርሳል፣ መድረሳቸውን ያረጋግጣል፣

9) በጉባኤው ወይም በንኡስ አጣሪ ኮሚቴው ለጉባኤ አባላት እንዲደርሱ የተወሰኑ ሰነዶችንና አጀንዳዎችን ያደርሳል፣ መድረሳቸውን ያረጋግጣል፡፡

10) ከጉባኤው ሰብሳቢ፣ ም/ሰብሳቢ አና ከንኡስ አጣሪ ኮሚቴው ሰብሳቢዎች የስራ መመሪያ ይቀበላል፣

11) ጉባኤው፣ ንኡስ አጣሪ ኮሚቴው አና የጉባኤው አባላት የተሰጣቸውን ተግባርና ሀላፊነት በብቃት እንዲያከናውኑ አጠቃላይ ድጋፍ ይሰጣል፣

12) ከጉባኤው ሰብሳቢ ጋር በመመካከር ለጉባኤው የሚደርሱ ጥሪዎችና ግብዣዎች ላይ ጉባኤውን ወክለው የሚገኙትን አንዲሁም ጉባኤውን ለመጎብኘት የሚመጡት እንግዶች የሚስተናገዱበትን ስርዓት ይወስናል፡፡

13) የጉባኤውን አባላት እና የጽ/ቤቱ ሃላፊዎችና ሰራተኞች የውጭ ጉዞዎች ለጉባኤው ሰብሳቢ አቅርቦ ያስፈቅዳል፡፡

## ክፍል አራት

## የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄዎችና አቤቱታዎች አቀራረብና የማጣራት ሂደት

### 13. ለጉባኤው የሚቀርብ የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ወይም አቤቱታ ይዘት

1) በፍ/ቤት በመታየት ላይ የሚገኝ ጉዳይን አስመልክቶ የሚቀርብ የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ፤

ሀ) በፍርድ ቤቱ የቀረበ ከሆነ የፍ/ቤቱን ወይም የችሎቱን ስምና አድራሻ፣ የዳኛውን ወይም የዳኞቹን ስም፣ የተከራካሪዎቹን ስም፣ የመዝገብ ቁጥሩን፣ በፍ/ቤቱ የተያዘው ጉዳይ ምንነት በአጭሩ፣ ፍ/ቤቱ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል ያለውን የሕግ ነጥብ ማብራሪያ እና የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልጋል ያለበትን ምክንያት በአጭሩ፤

ለ) ከባለጉዳዮቹ በአንዱ የቀረበ ከሆነ የፍ/ቤቱን ወይም የችሎቱን ስምና አድራሻ፣ የተከራካሪዎቹን ስምና አድራሻ፣ የመዝገብ ቁጥሩን፣ በፍ/ቤቱ የተያዘው ጉዳይ ምንነት በአጭሩ፣ የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄው በፍርድ ቤቱ በኩል እንዲቀርብለት ጠይቆ ተቀባይነት ያላገኘ መሆኑን፣ ጥያቄው በፍርድ ቤቱ ውድቅ የሆነበትን ቀን እና የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልጋል ያለበትን የሕግ ነጥብ ማብራሪያ እና የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልጋል ያለበትን ምክንያት በአጭሩ መቅረብ አለበት።

2) በመንግስት አካላት ወይም ባለስልጣን የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ ጉዳይ ህገ መንግስታዊነትን አስመልክቶ የሚቀርብ አቤቱታ ከሆነ የአመልካችና ተጠሪ ስምና አድራሻ፣ አቤቱታ የቀረበበት ቀን፣የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልጋል ያለበትን ምክንያት በአጭሩ፣ በየደረጃው የተሰጡ ውሳኔዎችን በቅደም ተከተል አባሪ ተደርጎ መቅረብ አለበት።

3) በፌዴራል፣ በክልል ወይም በከተማ አስተዳደር ህግ አውጪ አካላት የወጣ ህግን ወይም የክልል ሕገ መንግስት ሕገ መንግስታዊነት ጥያቄ ላይ የቀረበ ከሆነ የሕገ መንግስት ጥያቄ የቀረበበት ህግ ወይም ሕገ መንግስት አጭር ርዕስ፣ ህጉ የወጣበትን ቀን፣ የአመልካችን ስምና አድራሻ፣ የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ የቀረበበት ድንጋጌ፣ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልጋል የተባለበትን ምክንያት በአጭሩ እና ትርጉም የተጠየቀበት ሕግ አባሪ ተደርጎ መቅረብ አለበት።

4) በመንግስት አካላት የሚቀርብ የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ወይም አቤቱታ ከሆነ የአቅራቢውን የመንግስት አካል ስም፣ ሕጋዊ ማሕተምና አድራሻ፣ የመንግስት አካሉ

የበላይ ሃላፊ ወይም ወኪል ስምና ኃላፊነት፣ በጉዳዩ ተጠሪ ካለ የተጠሪውን ስምና አድራሻ፣ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል የተባለበትን ምክንያት በአጭሩ መያዝ አለበት።

5) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1(ለ) ለአጣሪ ጉባኤው የቀረበ የህገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ በፍርድ ቤት ያለው ጉዳይ በእንጥልጥል እንዲቆይ ጉባኤው ሊያዝ ይችላል።

14. የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ወይም አቤቱታ አቀራረብ፣

1) የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ወይም አቤቱታ የሚቀርበው በጽሁፍ ሲሆን በፌዴራል መንግስት የስራ ቋንቋ ይሆናል። ከሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄው ወይም አቤቱታው አባሪ ተደርገው የሚቀርቡ ሰነዶች በፌዴራል መንግስት የስራ ቋንቋ ተተርጉመው መቅረብ አለባቸው።

2) ለጉባኤው የሚቀርብ የህገ መንግስት ትርጉም አቤቱታ ወይም ጥያቄ የጉባኤው ስምና አድራሻ፣ የአቤቱታውን ርዕስና የአመልካቹን ፊርማ መያዝ አለበት።

3) በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚቀርብ የህገ መንግስት ትርጉም አቤቱታ ወይም ጥያቄ በባለ ጉዳዩ ወይም በወኪሉ ሊቀርብ ይችላል። በወኪል የሚቀርብ ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የውክልና ማስረጃ ተያይዞ መቅረብ አለበት።

4) አቤቱታውን ወይም ጥያቄውን ያቀረበው ሰው አቤቱታው ወይም ጥያቄው በእውነት የቀረበ ስለመሆኑና ጉዳዩ ከዚህ በፊት ለጉባኤው ያልቀረበ ስለመሆኑ ማረጋገጥ አለበት።

5) አቤቱታው ወይም ጥያቄው አስጽያፊና ለሕዝብ ሞራል ተቃራኒ የሆነ አገላለጽ ወይም አላስፈላጊ ዝርዝር ነገሮች ወይም ከጉዳዩ ጋር ተዛማጅነት የሌላቸው ነገሮች መያዝ የለበትም።

6) ጉባኤው በቀረበው የሕገ መንግስት ትርጉም አቤቱታ ወይም ጥያቄ ላይ በጽሁፍ መልስ ወይም አስተያየት እንዲሰጥ የወሰነ እንደሆነ የሚቀርበው መልስ ወይም አስተያየት በዚህ አንቀጽ እና በአንቀጽ 13 የተዘረዘሩ መስፈርቶችን እንደአግባብነቱ አሟልቶ መያዝ አለበት።

## 15. ተቀባይነት ስለሌላቸው የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄዎች እና አቤቱታዎች አወሳሰን

1) የጉባኤው ሬጅስትራር የሚቀርብለትን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ፣ አቤቱታ ወይም መልስ ወይም አስተያየት በአንቀጽ 13 እና 14 መሰረት የተቀመጡ መስፈርቶችና ሁኔታዎችን አሟልቶ ያልቀረበ ከሆነ ላይቀበል ይችላል፡-

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ አንድ መሰረት ውድቅ የተደረገ አቤቱታ፣ ጥያቄ፣ መልስ ወይም አስተያየት ተሟልቶ ሲቀርብ እንደገና ለጉባኤው መቅረብ ይችላል፡፡

3) ንኡስ አጣሪ ኮሚቴው በሚከተሉት ምክንያቶች የቀረበለትን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ወይም አቤቱታ ላይቀበል ይችላል፡-

   ሀ) የቀረበው ጉዳይ የመጨረሻ ውሳኔ አላገኘም ብሎ ያመነ ከሆነ፣

   ለ) ጉባኤው በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ወይም የውሳኔ ሀሳብ ተሰጥቶበት የነበረ ከሆነና በአዲሱ አቤቱታ የቀረበው ጉዳይ ምንም ተጨማሪ አዲስ ነገር ያልያዘ ከሆነ፣

   ሐ) የቀረበው አቤቱታ ወይም ጥያቄ ይዘት ሕገ መንግስታዊ ጉዳይ ካልሆነ፣

4) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3 መሰረት ተቀባይነት ያላገኘ አቤቱታ ወይም ጥያቄ ለጉባኤው ቀርቦ መጽደቅ አለበት፡፡

## 16. የሕገ መንግስት አቤቱታዎች ወይም ጥያቄዎች ስለሚወሰኑበት ሁኔታ፣

1) በመንግስት አካላት ወይም ባለስልጣናት የመጨረሻ ውሳኔ ሕገ መንግስታዊ መብቴ ወይም ነጻነቴ ተጥሷል የሚል ማንኛውም ሰው የሕገ መንግስት አቤቱታ ወይም ጥያቄ ለጉባኤው ማቅረብ ይችላል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ መሰረት የቀረበው አቤቱታ ወይም ጥያቄ ንኡስ አጣሪ ኮሚቴው መርምሮ የሕገ መንግስት ጉዳይ ባለመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም ሲል በሙሉ ድምጽ ሊወስን ይችላል፡፡ ሆኖም ከንኡስ አጣሪ ኮሚቴው አባላት መካከል አንዱ የቀረበው ጉዳይ ተቀባይነት ሊኖረው ይገባል የሚል የልዩነት ሃሳብ ያለው ከሆነ አቤቱታው ተጨማሪ ምርመራ ተደርጎበት የአብላጫውና የልዩነት ሃሳቦች ቀርበው ጉዳዩ በጉባኤው የሚወሰን ይሆናል፡፡

3) የቀረበው የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ የፌደራል፣ የክልል፣ የከተማ አስተዳደር ህግን እንዲሁም የክልል ሕገ መንግስት ሕገ መንግስታዊነት ወይም ሌሎች የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄዎችን የሚመለከት ከሆነ ጉዳዩ በንኡስ አጣሪ ኮሚቴው

ተጣርቶ በተዘጋጀው አስተያየት ላይ በመመስረት ውሳኔ የሚሰጠው በጉባኤው ነው፡፡

4) በዚህ አንቀጽ መሰረት ንኡስ አጣሪ ኮሚቴው አቤቱታውን በመመርመር ትርጉም አያስፈልገውም በማለት በሙሉ ድምፅ ውሳኔ የሰጠበት ጉዳይ ለጉባኤው ቀርቦ ከጸደቀ በኋላ መዝገቡ ይዘጋል፡፡

## 17. ከፍ/ቤት የሚላኩ የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄዎች እና አቤቱታዎች ስለሚወሰኑበት ሁኔታ

1) የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ወይም አቤቱታ በፍ/ቤት ወይም በባለ ጉዳዩ ለጉባኤው ሲቀርብ ንኡስ አጣሪ ኮሚቴው ጥያቄው የሕገ መንግስት ጉዳይ ባለመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም በማለት በሙሉ ድምጽ ሊወስን ይችላል፡፡ ሆኖም ከንኡስ አጣሪ ኮሚቴው አባላት አንዱ የቀረበው ጉዳይ ተቀባይነት ሊኖረው ይገባል የሚል የልዩነት ሃሳብ ያለው ከሆነ ጥያቄው ወይም አቤቱታው ተጨማሪ ምርመራ ተደርጎበት የአብላጫውና የልዩነት ሃሳቦቹ በጽሁፍ ቀርበው ጉዳዩ በጉባኤው የሚወሰን ይሆናል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄው የቀረበው በፌደራል ጠ/ፍ/ቤት፣ በክልል ጠ/ፍ/ቤት ወይም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ከሆነ አጣሪ ኮሚቴው ጉዳዩን በመመርመር ለጉባኤው በዝርዝር አስተያየት እንዲቀርብ በማድረግ ጉባኤው እንዲወስን ያደርጋል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት ንኡስ አጣሪ ኮሚቴው አቤቱታውን መርምሮ ትርጉም አያስፈልገውም ሲል በሙሉ ድምፅ የተስማማበት ውሳኔ ለጉባኤው ቀርቦ መዝገቡ ይዘጋል፡፡

## 18. የሕገ መንግስት ትርጉም አቤቱታ ወይም ጥያቄ ስለሚቋረጥበት ሁኔታ

1) ማንኛውም የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ወይም አቤቱታ ጉባኤው በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በሚከተሉት ምክንያቶች በጉባኤው ሊቋረጥ ይችላል፡-

ሀ) ለጉዳዩ መቅረብ ምክንያት የሆነው ሕግ፣ ውሳኔ ወይም ድርጊት ቀሪ ከሆነ፣ ከተለወጠ ወይም ከተስተካከለ፣

ለ) አመልካች አቤቱታውን ወይም ጥያቄውን እንደተወ በጽሑፍ ከገለጸ፣ ወይም

ሐ) ሕጉ፣ ውሳኔው ወይም ድርጊቱ የሚመለከተው አካል በሚያቀርበው ጥያቄ መሰረት ሕጉ፣ ውሳኔው ወይም ድርጊቱ ከተስተካከለ እና መስተካከሉ በጉባኤው ሲረጋገጥ፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1(ሀ) መሰረት ጉባኤው ምርመራውን ያቋረጠው ድርጊቱ በሚመለከተው አካል ጥያቄ አቅራቢነት የሆነ እንደሆነ ጉባኤው ጉዳዩን ማጣራቱን የሚያቋርጠው ጠያቂው ተቋም ማስተካከያ ለማድረግ ለሚያስችለው ጊዜ ብቻ ይሆናል፡፡ ስለሆነም ጠያቂው ተቋም በተሰጠው ጊዜ ማስተካከያ የማያደርግ ከሆነ ጉባኤው ጉዳዩን ማጣራቱን ካቆመበት ይቀጥላል፡፡

3) ጉባኤው በንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ለጉዳዩ መቅረብ ምክንያት የሆነው ሕግ፣ ውሳኔ ወይም ድርጊት የሚመለከተው አካል ጠርቶ እንዲያስተካክል ሊጠይቀው ይቻላል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ንኡስ አጣሪ ኮሚቴው ወይም ጉባኤው ተገቢ ነው ብሎ ካመነ አቤቱታው ወይም ጥያቄው እንዳይቋረጥ ወይም የተቋረጠው የማጣራት እና ውሳኔ አሰጣጥ ሂደቱ እንዲቀጥል ሊወስን ይችላል፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1(ለ) መሰረት የተቋረጠ የሕገ መንግስት ትርጉም አቤቱታ ወይም ጥያቄ አሳማኝ በሆነ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በድጋሚ ለጉባኤው ቀርቦ ሊታይ አይችልም፡፡

## ክፍል አምስት

## የንኡስ አጣሪ ኮሚቴውና የጉባኤው የውይይትና የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት

### 19. ስለ ንኡስ አጣሪ ኮሚቴ ስብሰባ፣

1) ከግማሽ በላይ የንኡስ አጣሪ ኮሚቴው አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

2) የንኡስ አጣሪ ኮሚቴው አባላት በያዟቸው ጉዳዮች ላይ በቋሚነት በመገናኘት የሚወያዩባቸውን የሳምንቱን ቀናት ይወስናሉ፡፡ ሆኖም አጣዳፊ ጉዳዮች ሲኖሩ በኮሚቴው ሰብሳቢ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡

### 20. የንኡስ አጣሪ ኮሚቴው የውይይትና ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት፣

1) ኮሚቴው በተመራለት የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ወይም አቤቱታ ላይ አስተያየት ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡

2) ኮሚቴው በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት በቀረበው አስተያየት ላይ ውይይት ካደረገ በኋላ በተጨማሪነት መታየት ያለባቸው ጉዳዮች ካሉ በመለየት አስተያየቱ ተሻሽሎ እንዲቀርብ መመሪያ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ነገር ግን የቀረበው አስተያየት በቂ

ሆኖ ካገኘው እንደአግባብነቱ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል ወይም ለጉባኤው አስተያየት ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡

3) ንኡስ አጣሪ ኮሚቴው ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ ይሰጣል፡፡ እኩል ድምጽ ከሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን አብላጫ ድምጽ እንደሆነ ይቆጠራል፡፡

4) ኮሚቴው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የሕገ መንግስት ትርጉም አቤቱታዎች ወይም ጥያቄዎች አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ የትርጉም ጥያቄን የሚያስነሱ ሆነው ካገኘው ተጣምረው እንዲጣሩ ሊያደርግ ይችላል፡፡

5) ኮሚቴው የቀረበለትን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ወይም የሕገ መንግስት አቤቱታ በዚህ መመሪያ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ያልተቀበለው ከሆነ የውሳኔውን ምክንያት በአጭሩ በጽሁፍ መግለጽ አለበት፡፡

6) ኮሚቴው በአንድ የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ላይ መወያየት ከጀመረ በኋላ የኮሚቴ አባል ከተቀላቀለ አባሉ መሳተፍ ከመጀመሩ በፊት በተደረጉት ውይይቶች ላይ በኮሚቴው ሰብሳቢ በቂ ገለጻ ይደረግለታል፡፡

7) የኮሚቴው ሰብሳቢ የኮሚቴው አባላት በቀረበው ጉዳይ ላይ ከተወያዩ በኋላ አባላቱ አንድ በአንድ ድምጽ እንዲሰጡ በማድረግ በመጨረሻ ራሱ ድምጽ ይሰጣል፡፡

8) ኮሚቴው ለጉባኤው የሚያቀርበው አስተያየት በተቻለ መጠን በጉዳዩ ውስጥ ባሉት በእያንዳንዱ ጭብጦች ላይ የሚያተኩር መሆን አለበት፡፡

## 21. የእግድ ጥያቄ አወሳሰን

1) ንኡስ አጣሪ ኮሚቴ የእግድ ጥያቄ ሲቀርብለት ጉዳዩን መርምሮ የህገ መንግስት ነጥብ ሊኖረው ይችላል ብሎ ካመነና በአመልካቹ ላይ የሚደርስን ሊተካ የማይችል ከፍተኛ ጉዳት ለማስቀም፣ በቅርብ ሊከሰት የሚችልን ሁከት ለማስቀረት ወይም በሌላ ለህዝብ ጥቅም አስፈላጊ በሆነ ምክንያት አንድ የሕገ መንግስት ጥያቄ የቀረበበት ሕግ፣ ልማዳዊ አሰራር፣ የመንግስት አካል ወይም ባለስልጣን ውሳኔ አፈጻጸም ጉዳዩን መርምሮ ውሳኔ ወይም የውሳኔ ሀሳብ እስኪሰጥ ድረስ ታግዶ እንዲቆይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

2) ንኡስ አጣሪ ኮሚቴው በሌላ አኳኋን ካልወሰነ በስተቀር በተሰጠ እግድ ላይ እግዱ እንዲነሳ የሚቀርብ አቤቱታ የእግዱን አፈጻጸም እንዲቋረጥ አያደርግም፡፡

## 22. የጉባኤው የውይይት እና የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት፣

1) አንድ የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ወይም አቤቱታ በጉባኤው ውይይት የሚደረግበት ጉዳዩ አስቀድሞ በንኡስ አጣሪ ኮሚቴው ከታየ በኂላ ነው፡፡ ሆኖም አስፈለጊ ሆኖ ሲገኝ ጉዳዮች በቀጥታ ለጉባኤው ቀርበው ሊታዩ ይችላሉ

2) ጉባኤው በቀረቡለት አስተያየቶች ላይ ውይይት የሚያደርገው በጉዳዮቹ የአቀራረብ ቅደም ተከተል ላይ በመመስረት ነው፡፡ ሆኖም፡-

   ሀ) አቤቱታው የአገርና የሕዝብን ጥቅም የሚመለከትና ለአጠቃላይ ሕገ መንግስታዊ ስርአት መጎልበት ጠቀሜታ ያለው ከሆነ፣

   ለ) ጉዳዩ የህጻናትን፣ የሴቶችን፣ ተከሰው በእስር ላይ ያሉ ሰዎችን፣ የአካልና የዓእምሮ ጉዳተኞችን፣ የአረጋውያን መብት በቀጥታ የሚመለከት ከሆነ፣

   ሐ) በጉዳዩ ላይ እግድ የተሰጠበት ከሆነ ወይም በሌላ አሳማኝ ምክንያት፣

   የጉባኤው ሰብሳቢ በሚወስነው መሰረት ጉዳዮች ቅድሚያ ሊሰጣቸው ይችላል፡፡

3) ጉባኤው በአንድ የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ወይም አቤቱታ ላይ መወያየት ከጀመረ በኂላ የጉባኤ አባል ከተቀላቀለ አዲስ የተቀላቀለው አባል መሳተፍ ከመጀመሩ በፊት በተደረጉት ውይይቶች ላይ በጉባኤው ሰብሳቢ በቂ ገለጻ ይደረግለታል፡፡

## 23. የጉባኤው ድምጽ አሰጣጥ ስርአት

1) ጉባኤው የቀረበው ጉዳይ በቂ ማጣራት የተደረገበትና አባላቱም በቂ ውይይት ተደርጎበታል ብለው ካመኑ በቀረበው ውሳኔ ወይም የውሳኔ ሃሳብ ላይ የጉባኤው ሰብሳቢ አንድ በአንድ ድምጽ እንዲሰጥበት ያደርጋል፡፡ በመጨረሻ የጉባኤው ሰብሳቢ ድምጽ ይሰጣል፡፡

2) ጉባኤው የሕገ መንግስት ትርጉም ውሳኔ ወይም የውሳኔ ሀሳብ ድምጽ የሚሰጠው አባላቱ ብቻ በተገኙበት በዝግ ስብሰባ ነው፡፡

3) ጉባኤው ውሳኔ ወይም የውሳኔ ሀሳብ የሚሰጠው በአብላጫ ድምጽ ነው፡፡ የተሰጠው ድምጽ እኩል የተከፈለ ከሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን የጉባኤው ውሳኔ ይሆናል፡፡

## 24. መልስ ወይም አስተያየት ስለመጠየቅ፣

1) ጉባኤው በአንድ ጉዳይ ላይ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል የሚል እምነት ካሳደረ የተጠሪን መልስ ወይም አስተያየት መቀበል ይችላል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ መሰረት መልስ ወይም አስተያየት እንዲሰጥ የተጋበዘ ሰው ወይም የመንግስት አካል በተፈቀደለት ጊዜ ውስጥ መልስ ወይም አስተያየት ያላቀረበ ከሆነ ንኡስ አጣሪ ኮሚቴው ወይም ጉባኤው በቀረበለት ሰነድ ላይ ተመስርቶ ተገቢውን የማጣራት ተግባር ያከናውናል፡፡

## 25. ባለጉዳዮችን ስለመስማት

1) ጉባኤው ወይም ንኡስ አጣሪ ኮሚቴው ለሚያካሄደው ማጣራት አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ባለጉዳዮችን አስቀርቦ ሊሰማ ይችላል፡፡

2) ጉባኤው በመስማት ሂደቱ የአሰማሙን አካሄድና የሚሰሙ ጭብጦች ወይም የአትኩሮት ጉዳዮች በተመለከተ ለባለጉዳዮች ሊያሳውቅ ይችላል፡፡ የመስማቱ ሂደት በድምጽ ተቀርጾ ለጉባኤው አገልግሎት እንዲውል ሊደረግ ይችላል፤ ይህም እንደሚደረግ ለባለጉዳዮች መሰማቱ ከመጀመሩ በፊት ይገለጽላቸዋል፡፡

3) ጉባኤው ጉዳዩን ለማጣራት አስፈላጊ የመሰለውን የማጣሪያ ጥያቄዎች ማቅረብ ይችላል፡፡

## 26. የሙያ አስተያየት ስለመሰብሰብ

1) ጉባኤው የቀረበለትን ጉዳይ ለመወሰን አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን ከጉዳዩ ጋር ተዛማጅነት ባላቸው የሙያ ዘርፍ የሚሰሩ ባለሞያዎች፣ የሕግ ምሁራን፤ የመንግስት ተቋማት ወይም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በጽሁፍ እና/ወይም በቃል *የአሚከስ ኩሪ* (Amicus Currie) አስተያየት እንዲያቀርቡ ሊጋብዝ ወይም በራሳቸው አነሳሽነት ከጠየቁ አስተያየታቸውን እንዲያቀርቡ ሊፈቅድላቸው ይችላል፡፡

2) ጉባኤው ለውሳኔ ወይም ውሳኔ ሀሳብ ለመስጠት አስፈላጊ ነው ብሎ ያመነበትን ማንኛውንም አይነት ማስረጃ አስቀርቦ ሊመረምር ይችላል፡፡

## 27. የልዩነት ሃሳብ

1) በጉባኤው ውሳኔ የሃሳብ ልዩነት ያለው የጉባኤ አባል ልዩነቱን በጽሁፍ ያሰፍራል፤ ጽሑፉም ለጉባኤው በንባብ ከቀረበ በኋላ የውሳኔ ሀሳቡ አካል ይሆናል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተው የሃሳብ ልዩነት ያለው አባል ጉባኤው በጉዳዩ ላይ ከውሳኔ በደረሰ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ አዘጋጅቶ ለጉባኤው ሰብሳቢ መስጠት አለበት፡፡ ይህ ጊዜ አስፈላጊ ከሆነ በአንድ ተጨማሪ ሳምንት ሊራዘም ይችላል፡፡

## 28. የውሳኔ እና ውሳኔ ሀሳብ አዘገጃጀትና ይዘት

1) ጉባኤው በቀረበለት የሕገ መንግስት ትርጉም አቤቱታ ወይም ጥያቄ ላይ በሚሰጠው የውሳኔ ሀሳብ የተጣሰውን የሕገ መንግስት ድንጋጌ እና ድንጋጌውን የጣሰውን ድርጊት ወይም የድርጊት አለመፈጸም በግልጽ ማመልከት አለበት፡፡

2) የሕገ መንግስት ትርጉም አቤቱታው መነሻ የፍርድ ቤት ውሳኔ ከሆነ ጉባኤው አቤቱታውን ካጣራ በኋላ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ካገኘው ውሳኔውን በመሻር ጉዳዩ ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ተመልሶ በአግባቡ እንዲወሰን እንዲደረግ ለፌደሬሽን ም/ቤት የውሳኔ ሃሳብ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

3) የአንድን ሕግ ሕገ መንግስታዊነት የሚመለከት የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ተቀባይነት ካገኘ ጉባኤው ሕጉ ወይም የሕጉ ክፍል እንዲሰረዝ የውሳኔ ሃሳብ ለፌደሬሽን ምክር ቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) መሰረት እንዲሻር አስተያየት የቀረበበት የፍ/ቤት ውሳኔ ሕገ መንግስቱን በሚጻረር ሕግ ላይ ተመስርቶ የተሰጠ ውሳኔ ከሆነ ሕጉ ወይም የሕጉ ክፍል እንዲሰረዝ ጉባኤው ለፌደሬሽን ምክር ቤት አስተያየት ያቀርባል፡፡

5) በጉባኤው የሚሰጠው ውሳኔ ወይም የውሳኔ ሃሳብ መግቢያ፣ ዋና ክፍል እና የውሳኔ ወይም የውሳኔ ሃሳቡ ዝርዝር የአፈጻጸም ወይም የአተገባበር አስተያየት ትንታኔ የያዙ ክፍሎች ይኖሩታል፡፡ ጉዳዩ ከአንድ በላይ ጭብጦች ያሉት ከሆነ በውሳኔው ወይም በውሳኔ ሃሳቡ ዋና ክፍል እያንዳንዱ ጭብጥ ተተንትኖ መወሰን ይኖርበታል፡፡

6) በጉባኤው ውሳኔ ወይም የውሳኔ ሀሳብ ላይ ከሰብሳቢውና ምክትል ሰብሳቢው ቀጥሎ ያሉት የጉባኤው አባላት በጉባኤው የአገልግሎት ዘመናቸው ቅደም ተከተል ስማቸው ይጻፋል፡፡ እኩል የአገልግሎት ዘመን ያላቸው አባለት በስማቸው ፊደል ተራ ቅደም ተከተል ስማቸው ተጽፎ በእያንዳንዱ ገጽ ላይ ይፈርማሉ፡፡

7) ጉባኤው በአንድ ጉዳይ ላይ የውሳኔ ሀሳብ ከሰጠ በኋላ ውሳኔውንና መዝገቡን ለፌደሬሽን ም/ቤት መላክ አለበት፡፡

# ክፍል ስድስት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 29. የጉባኤ አባል ከማጣራት ተግባር ስለሚነሳበት ሁኔታ

1) አንድ የጉባኤ አባል ከዚህ ቀጥሎ ከተመለከቱት ምክንያቶች በአንዱ ከሕገ መንግስታዊ ጉዳዮች ማጣራት ሊነሳ ይችላል፡-

ሀ) ከባለጉዳዮቹ ከአንደኛው ወገን፣ ከጠበቃው ወይም ከወኪሉ ጋር የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው ከሆነ፣

ለ) ከባለጉዳዮቹ የአንደኛው ወገን ሞግዚት፣ ነገረ ፈጅ ወይም ጠበቃ በሆነበት ጉዳይ ላይ የተነሳ አቤቱታ ወይም ጥያቄ የሆነ እንደሆነ፣

ሐ) አቤቱታ ወይም ጥያቄ የተነሳበትን ጉዳይ አስቀድሞ በዳኝነት ወይም በዕርቅ መንገድ ያየው ወይም የሚያውቀው ከሆነ፣

መ) ከባለጉዳዮቹ ከአንደኛው ወይም ከጠበቃው ጋር በፍርድ ቤት የተያዘ ክርክር ወይም ሙግት ያለው እንደሆነ፣

ሠ) በዚህ ንኡስ አንቀጽ ከተመለከቱት ምክንያቶች ውጭ ትክክለኛ ፍትሕ አይሰጥም የሚያሰኝ ሌላ በቂ ምክንያት ሲኖር ነው፡፡

2) አንድ የጉባኤ አባል በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት የተቀመጡ ሁኔታዎች መኖራቸውን ሲያውቅ ከማጣራት ሂደት እንዲነሳ ጉባኤውን መጠየቅ አለበት፡፡

3) በዚህ አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ 2 የቀረበለትን ጥያቄ መሰረት ጉባኤው በሕገ መንግስቱ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት እና የአቤቱታውን ይዘት ከግምት ውስጥ በማስገባት አባሉ እንዲነሳ ሊወስን ይችላል፡፡ የቀረበው ጥያቄ በንኡስ አጣሪ ኮሚቴ አባል ሲሆን ውሳኔው የሚሰጠው በንኡስ አጣሪ ኮሚቴው ነው፡፡

4) በዚህ አንቀጽ መሰረት አንድ የጉባኤ አባል ገለልተኛ አይደለም የሚል አቤቱታ በባለጉዳይ የቀረበበት ሲሆን ጉባኤው በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀፅ (1) የተጠቀሱት ሁኔታዎች መኖራቸውን በማረጋገጥ የጉባኤውን አባል በዚያ ጉዳይ የማጣራት ስራ ውስጥ እንዳይሳተፍ ሊያደርግ ይችላል፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4 በባለጉዳይ የሚቀርበው ማመልከቻ ማጣራቱ ከመጀመሩ በፊት ወይም ማመልከቻ ለማቅረብ ምክንያት መኖሩን አመልካቹ እንዳወቀ ወዲያውኑ መሆን አለበት፡፡

**30. የጉባኤው አባላት ሃላፊነት**

ማንኛውም የጉባኤ አባል፣

ሀ) በበቂ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በማንኛውም የጉባኤ ስብሰባ በሰዓቱ መገኘት፣

ለ) በበቂ ምክንያት ስብሰባ የማይገኝ ከሆነ ይህንኑ ለጉባኤው ሰብሳቢ ወይም ለጽ/ቤቱ ሃላፊ አስቀድሞ ማሳወቅ፣

ለ) በጉባኤው ስብሰባ በአጀንዳነት በተያዘ ጉዳይ ላይ በቂ ዝግጅት አድርጎ መገኘት እና መሳተፍ፣

ሐ) ሕገ መንግስቱን ማክበርና ማስከበር፣ በገለልተኛነት እና በነጻ ህሊና ሀላፊነቱን መወጣት፣

መ) የጉባኤውን መልካም ስምና ክብር የመጠበቅና የማስጠበቅ፣

ሠ) ይህንን መመርያ የማክበር እና የማስከበር ግዴታ አለበት፡፡

## 31. የጉዳዮችን ሚስጥራዊነት ስለመጠበቅ

የጉባኤው አባላትና ሰራተኞች ውሳኔ ያላገኙና በሂደት ላይ ያሉ ጉዳዮችን በሚመለከት ለሶስተኛ ወገን መረጃ መስጠት፣ ትምህርታዊ ለሆኑ ጉዳዮች መጠቀም፣ እንዲሁም ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሰነዶች ከጉባኤው አባላትና ባለሞያዎች ውጪ ለሌላ ሰው መስጠት የለባቸውም፡፡

## 32. የጉዳዮች ፋይል አያያዝ

የአንድን ጉዳይ የማጣራት ሂደት የሚመለከቱ ሰነዶች በጉዳዩ ፋይል ውስጥ ተመዝግበው መያዝ አለባቸው፡፡ ሆኖም ውሳኔ፣ የውሳኔ ሀሳብ፣ የዝግጅት ሰነዶችና የድምጽ አሰጣጥ ሂደትን የሚያሳዩ ሰነዶች በጉዳዩ ፋይል ውስጥ አይቀመጡም፤ ለብቻ በተሸፈነ መያዣ ውስጥ ተደርገው ይቀመጣሉ፡፡

## 33. ስለ ክፍያ

የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄዎች ከክፍያ ነጻ ናቸው፡፡ ነገር ግን የሕገ መንግስት ትርጉም አቤቱታን ወይም ጥያቄን ከቅን ልቦና ወጪ የሚጠቀም አመልካች ወይም ማናቸውም ሌላ ሰው በአጣሪ ኮሚቴው አቅራቢነት በጉባኤው የገንዘብ ቅጣት ሊጣልበት ይችላል፡፡

## 34. የጉባኤው የውይይትና የስብሰባ ጊዜ

የጉባኤው የውይይትና የስብሰባ ጊዜ ከአገሪቱ መደበኛ ፍ/ቤቶች የስራ ጊዜ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ሆኖም ጉባኤው በጽ/ቤቱ ያለው የስራ ጫና ግምት ውስጥ በማስገባት በእረፍት ጊዜው ተጨማሪ ስብሰባዎችን ሊጠራ ይችላል፡፡

## 35. ስለ ሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት

1) የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ በዚህ መመሪያ ውስጥ ያልተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት እንደአግባብነቱ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

2) ይህን መመሪያ የሚቃረን ማናቸውም ሕግ እና የአሰራር ልምድ መመሪያው በተደነገገባቸው ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

## 36. መመሪያውን ስለማሻሻል

1) ማንኛውም የጉባኤው አባል ይህ መመሪያ እንዲሻሻል ሃሳብ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተው የማሻሻያ ሃሳብ መቅረብ ያለበት በጽሁፍ ሆኖ የሚሻሻለውን የመመሪያው ክፍል ከነምክንያቱ እና በተተኪነት የቀረበውን የማሻሻያ ሃሳብ የያዘ መሆን አለበት፡፡

3) የቀረበው የማሻሻያ ሃሳብ ለጉባኤው ቀርቦ በአብላጫ ድምፅ ተቀባይነት ካገኘ ተግባር ላይ ይውላል፡፡

## 37.የመመሪያው ተፈጻሚነት

ይህ መመሪያ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አዋጅ ቁ. 798/2005 አንቀጽ 33 መሰረት በጉባኤው ከጸደቀበት ከዛሬ ሐምሌ 22 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ወ/ሮ መዓዛ አሸናፊ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ሰብሳቢ